# አ ት ሮ ን ስ ዘ ተ ዋ ሕ ዶ

ደግ ሰው ነህን?
ደግ ሰው: በሚገባ! መልካም ለመስራት እሞክራለሁ!
ካህን※ አስርቱን ትእዛዛት ጠብቀሃልን?<br>
ደግ ሰው: በሚገባ ነዋ
ካህን※ መልካም! ብናያቸው ፍቃደኛ ነህ?
ደግ ሰው: ይቻላል!
ካህን※ ዋሽተህ ታውቃለህ?
ደግ ሰው: አዎ! የማይዋሽ ማን አለ?
ካህን※ እየደጋገመ የሚዋሽ ሰው ምን ይባላል ?
ደግ ሰው: የውሽት አባት ውሽታም!
ካህን※ ሰርቀህ ታውቃለህ?
ደግ ሰው: ኖ ኖ ኖ
ካህን※ ነገር ግን ውሽታም እንደሆንክ ነግረኸኛል
ደግ ሰው: በእርግጥ ልጅ እያለሁ ከረሜላ ሰርቄያለሁ!
ካህን※ የሚሰርቅ ሰው ምን ይባላል?
ደግ ሰው: ሌባ!
ካህን※ በምኞት ወደ ሴት ልጅ አይተሃል?
ደግ ሰው: በሚገባ ነዋ!
ካህን※ ወንጌል አይቶ የተመኘ በልቡ አመነዘረ ይልሃል በራስህ ቃል መሰረት ውሽታም ሌባና ልበ ዘማዊ ነህ። እነዚህ ደገሞ ከአስርቱ ትእዛዝ ሶስቱ ናቸው
ደግ ሰው: እንከን የሌለበት ሰው አይደለሁም ማለተ ነው!
ካህን※ የሰራኸውንና የምታስበውን ነገሮች ሁሉ የሚቀርጽ ካሜራ በአእምሮህ ውስጥ እንዳለ አስብና እስኪ ሳምንቱን ሙሉ የቀዳኸውን ለጓደኞችህ ለቤተሰቦችህም እንደ ፊልም አሳያቸው!
ደግ ሰው: ይህማ ታላቅ ውርደት ነው! በ ፍፁም አላደርገውም!!!
ካህን※ እግዚአብሄር ግን የልብን ያውቃል!
ደግ ሰው: ከአልቃይዳና ከአክራሪዎች አንፃር እኔ ደግ ነኝ!
ካህን※ ልክ ነህ ይህ ግን የፈጣሪ ህግ እንጂ የሰው ህግ አይደለም በቀን 5 ጊዜ ብቻ ብትዋሽ በአመት 5 ※ 365 = 1825 ጊዜ ትዋሻለህ ማለት ነው ፡ የፈጣሪንም ህግ ጥሰሃልና ቅጣት ይጠብቅሃል
ደግ ሰው: ፈጣሪ ለምን ዝም ብሎ ይቅር አይለኝም?
ካህን※ ይህን ፍርድ ቤት ሞከረው
ደግ ሰው: ክቡር ዳኛ ሆይ ደጋግሜ ህግ መጣሴን አውቃለሁ! ይቅር ብዬሃለሁ ማለት አትችልም?
ካህን※ ሙሰኛ ዳኛ ብቻ በነፃ ይለቅሃል መልካም ዳኛ ግን ለወንጀልህ ትክክለኛውን ፍርድ ይሰጥሃል እግዚአብሄር የፍትህ ዳኛ ነው። ሃጢአትን ይጠላል ሃጢአተኛ ወደሚንበለበለው ዘላለማዊ እሳት ይጣላል በዚያም ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል
ደግ ሰው: ጉድ ፈላ! ታድያ ማን ሊድን ይችላል?
ካህን※ በፍርድ ቀን ለምን ሃጢአት ሰራህ አትባልም ለምን ንስሃ አልገባህም ትባላለህ እንጂ በቶሎ ንስሃ ግባ ትእዛዛቱን ጠብቅ ደግ ሰው ሆይ መልካም ዘር ዝራ መልካም ፍሬን ታገኛለህና! ✿ራይ 2፣5 እንግዲህ ከወዴት እደወደቅ አሰብ ንሰሐም ግባ
ደግ ሰው ሆይ ደግ ሰርተህ ደገኛይቱን መንግሥት ትወርስ ዘንድ የክርስቶስ ፈቃድ ይሁንልን::




እኛስ የት ነን ንስሐ ገብተን ስጋውን በልተን ደሙን ጠጥተን እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ትዕዛዙን ጠብቀን ነው ወይስ ዓለም ለራሷ አስገዝታን በኃጢኣት በሽታ ተይዘን ወድቀን መድሐኒት ክርስቶስን በስም ብቻ ይዘን ነው ያለነው። በመሠረቱ ሰው ሆኖ የማይበድል የለም ። ሰው ኃጢአት ከሠራ በደልንም ከፈጸመ ለሠራው ኃጢአትና በደል አጸፋው ሞት መሆኑን አውቆ ራሱን በጸጸት፣ ብሎም የንስሐው ሥርዓት በሚያዝዘው መሠረት ራሱን ለቅጣት ማዘጋጀት ይኖርበታል። ይህ በማድረጉ የእግዚአብሔር ቸርነት አጥርና ቅጥር ወይም ጋሻና መከታ ሁኖ ስለሚጠብቀው ዕድሜው ይረዝማለ፣ ሰላም ያገኛል፣ በመጨረሻም የኃጢአት ሥርየት ማግኘትና ርስተ መንግሥተ ሰማያትን የመውረስ ዕድልና ኃይል ይሰጠዋል።አንድ ሰው ጥፋተኛ ነኝ በደልን አድርጌያለሁ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስንም አፍረሻለሁ ብሎ መፀፀት ሲጀምር የኃጢአት ስር እየደረቀች ትሔዳለች ጭንጫ አሜኬላ ብቻ የሚያስብ የነበረውንም ልባችን የወይን እርሻ እንዳለ ማሰብ ይጀምራል።
ሥርየትና ይቅርታ ያላገኘ ወይም በንስሐ ያልተወገደ ኃጢአት የሰውን ኑሮ ለልዩ ልዩ መከራ አሳልፎ ከመስጠቱም በላይ ዕድሜን በማሳጠር ለንስሐ እንዳይበቁ የማድረግም ጠባይ አለው። ለዚህም ነው በኃጢአት ከወደቁ በኋላ ቶሎ መነሣትና ለንስሐ ሥርየት መዘጋጀት የሚያስፈልገው። እስቲ እግዚአብሔር የማንዋሸው ከሆን ስንቶቻችን የንስሐን ፍሬ አፍርተናል????
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- •“ንስሐ ግቡ፣ ኃጢአትም ዕንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ፤ የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ፤ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ፤ የእስራኤል ቤት ሆይ ሰለምን ትሞታላችሁ የምዋቹን ሞት አልፈቅድምና ይላል ጌታ እግዚአብሔር ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ” /ሕዝ. ፲፰፡፴-፴፪/።
”እንግዲህ ከወዴት እንደወደኽ ዐስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ። አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው አወስዳለሁ”ዮሐ ራዕይ ፪፥፭

ስለዚህ እንዘጋጅ ነገ ህይወት እንዳለ ሁሉ ሞትም መኖሩን እናስተውል። የንስሐ አባት የምትፈልጉ ወንድሞች አህቶች በውስጥ መስመር አግኙን @atronssbot

ይህን እዘዝና አስተምር። በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን እንጂ፥ ማንም ታናሽነትህን አይናቀው እስክመጣ ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ።
1ኛ ጢሞ ምዕ. 4፥11-13

" " " " " " " " "

https://telegram.me/atronss

አዘጋጅ፦ ብስራተገብርኤል ክፍሌ